
# <u>ሕዝብ ወደፊት ይወስናል?</u>

«ቸንክሮ የያዘሽ ካስማውና አውታሩ
ዓይነቱ ብዙ ነው ባድባሩ ባውጋሩ
ከቶ እንዴት እናርግሽ ልንፈታሽ ከስሩ?» ኃይሉ (ገሞራው)



የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘመናት ጭቆናውንና መብት ረገጣውን በጣጥሶ በሕዝብ አንድነትና እኩልነት ላይ የተመሠረተች ሀገሩን የራሱ ለማድረግ ከትግል ወደ ኋላ ያለበት ጊዜ የለም። እየተሰደደ፡ እየተገረፈ፡ እየታሰረ፡ እየተገደለ የድል ጊዜው ቢራዘምም የደረሰበትንና እየደረሰበት ያለውን ግፍና መከራ አሜን ብሎ አልተቀበለውም። አለንልህ እያሉት፡ ተስፋ እየመገቡት፡ አውላላ ሜዳላይ አንሳፈውት የሚኳዙት ከሀዲዎች ስሜቱን ቢፈታተኑትም ተስፋ መቁረጥን ተስፋው አላደረገም። ትላንትም ታግሏል፤ ዛሬም ይታገላል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የድል ፍሬ ማለት የዜግነት መብቱ መከበር ነው። የነገ ሀገር ተረካቢ የዛሬ ሕፃናት ልጆቹ ያለሰቀቀን የሚኖሩባት፡ በህንክብካቤ ቦርቀው፡ ባህላቸውን ጠብቀው የብሩህ ተስፋ ዜጋ ሆነው የሚያድጉባትን ኢትዮጵያ ማየት ነው ፍላጎቱ። ሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች በፍቅር፡ በእኩልነት፡ በአንድነት የሚኖሩባት፡ በልማትና ዕድገት ጎዳና የመሠማራት አንገብጋቢውና መሠረታዊ ጉዳይ ነው እምዬ ኢትዮጵያን ቀዳሚ አድርጎ ደሙን የሚያፈስላት፡ አጥንቱን የሚከሰክስላት።

በሀገራችን በግፈኛ፡ በአምባገነንና ዘረኛ አገዛዞች መብቱ ያልተረገጠ፡ በግፍ ሰንሰለት ያልተተበተበ፡ ለድህነት ለስቃይና በሽታ ያልተዳረገ የኅብረተሰብ ክፍል የለም። መንግስታት በተቀያየሩ ቁጥር በሀገርና ሕዝብ ላይ የሚደረገው መከራና ግፍ መጠን እየጨመረና መረን እየለቀቀ መምጣቱን እየታዘበ ያለው ሁሉም ዜጋ ነው። የነኚህ ግፈኛ አገዛዞች የጫኑብን መከራና ስቃይ ግን ሀገርን አላስረሳንም። ሀገር ላይ እንድናማርር፡ ሀገር ላይ እንድናነጣጥር አላደረገንም። ኦሮሞው፡ ትግሬው፡ ጉራጌው፡ አማራው፡ ሱማሌው፡ አፋሩ፡ ሁሉም እንደባህሉ በየቋንቋው ሀገሬ ኢትዮጵያ እያለ ተቀኝቶላታል። አንጎራጉሮላታል። ስለ ሀገር አንድነት እየዘመሩ የገደሉትንም ችሎ፡ "ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ተረት ተረት ናት" ብለው ያላገጡበትንና ኢትዮጵያዊ ስሜትን ሊቀብሩ ለተነሳሱት ሁላ ሳይበገር ሀገሩን በዝማሬው፡ በእንጉርጉሮው ከአፉ አለያትም። በሀዘን፡ በደስታው፡ በስፖርት ሜዳው፡ በሰልፉ፡ በስብሰባው፡ የሀገሩ መለያ ባንዲራ ከእቅፉ አልተለየም። የመከራው ገፈት ቢበዛበትም ኢትዮጵያ የማንነት መገለጫ መሆኗን ለአፍታም አልዘነጋም። ዳር ድንበርህ ተደፈረ ሲሉት በገረፉት ገዥዎች አዝማችነት እንኳ ዘምቶ ሀገርን በነጻነት አቆይቶልናል። ለዚህ ሁሉ የተከፈለው መስዋዕትነት ታዲያ መለያ ብሔሩን፡ ቋንቋውን፡ ባህሉን እንደያዘ ለኢትዮጵያዊነቱ ነው። በተለያዩ አገዛዞች የደረሰበትን ግፍና መከራ ሀገሩን እንዲጠላ አላደረገውም። ክብርና ኩራቱ፡ የማንነቱ መግለጫ ኢትዮጵያ ለመሆኗ ዘሩን ብቻ

እየመረጠ አልተጋባም፡ አልተዋለደም። ግዛት ከልሎ አልኖረም። አንዱ ብሔር/ብሔረሰብ ከሌላው ተጋብቶ የኖረባት፡ ጎጃም ያረሰውን ወለጋ የሸጠበት፡ የጅማን ቡና ሰሜን የጠጣበት፡ የወለጋን ጆቲ ሸዋ ያንጠለጠለበት፡ የድሬን ብርቱካን ወለጋ የላጠበት፡ የሐረር ሰንጋን ጉጂ የዘፈነበት፡ የደብረ ብርሃን አረቄን ቤኒሻንጉል የጨፈረበት፡ የጉራጌን ክትፎ ኦሮሞ ያጣጣመበት፡ የትግራይ አምባሻ ደቡብ የተጋገረበት፡ ለሲዳማ ቆንጆ አማራው ያዜመበት፡ አንዱ ካንዱ የተጎራረሰበት፡ አንዱ በሌላው ኩባያ የተጣጣበት፡ ሀገር ኢትዮጵያ እንደሀገር እንድትኖር ያደረገበት በደም የተሳሰረው የሁሉም ልጆቿ የሀገር ፍቅር ስሜት ነው። በአጥንት የተገነባው የጋራ ምሰሶ ነው። ለሁሉም ሳትጠብ አቅፋ የያዘች ኢትዮጵያ ትፈራርስ ዘንድ ፍላጎቱን ያሳየ የኅብረተሰብ ክፍል ከባዕድ ወራሪና ከሀዲ ባንዳዎች ሌላ ከቶም አይገኝም። ጭቆና፡ ብዝበዛ፡ ግድያ፡ ድህነት፡ በሽታ፡ ድንቁርና ኢትዮጵያዊ በመሆኑ የተሰጠው ገጸ በረከት እንዳልሆነ ሁሉም ጠንቅቆ ያውቀዋል። እስላም ክርስቲያኑን ባንድ ጎጆ ያኖረች፡ ለሙስሊሙ መብት ክርስቲያኑ የተዋደቀበት፡ እንዲሁ ለክርስቲያኑ ሙስሊሙ የተፋለመበት (ምሳሌ ራጉኤልን ያስታውሰዋል)፡ ሁሉን እንደ ሃይማኖቱ እያስተዳደረች፡ የበርካታ ቋንቋ ባለሀብት የሆነች፡ የራሷ ፊደል ያላት ብቸኛ አፍሪካዊት፡ የሉሲ ማደሪያ ዓለም የፃፈላት፡ ታሪኳ የልጆቿ ነውና እንከባከባት።

በአሁኑ ወቅት በተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጎራ ያለው አለመግባባትና ልዩነት በቀላሉ የማይታይ መሠረታዊ ልዩነት ነው። በጠላት አሰላለፍ ላይ ልዩነት ይታያል። ምን ዓይነት ለውጥ በሚለው ላይ የጎላ ልዩነት አለ። ሁሉም የዴሞክራሲን ካባ ተከናንቦ ውስጡን ሲመረምሩት ፡ ተግባራዊ ክንዋኔውን ሲመረምሩት ባዶና ውሸት እየሆነ መታዘብ ከጀመርን ውለን አድረናል። የጽሁፋቸውና የንግግራቸው ማጣፈጫ ጨው ይመስል ዴሞክራሲን እስኪያንገፈግፈን እየሰነቀሩ፡ መብቴ ነው እያሉ መብት ላይ የቆሙ ጊዜ የወለዳቸው የፖለቲካ ዓይነ ደረቆች በተለይ ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ ትርዕይት ወዲህ ስም እየቀያየሩ ድብብቆሽ ሲጫወቱ መታዘቡ መሰልቸት ብቻ ሳይሆን ያንገፈገፈ ጉዳይ ነው። ከአለፈው ስህተታቸው እየተማሩ ለእርምት ከመዘጋጀት ይልቅ ቀን በቆጠረ ቁጥር ልብ ማድረቃቸው እየጨመረና እያፈጠጠ የመጣበት ወቅት ላይ ደርሰናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ሁላ አጣብቂኝ ለመውጣት አሁንም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ስለ በሰበሰው የወያኔ አገዛዝ ውድቀት ብቻ ሳይሆን ስለ ቀጣዩ የሀገራችን መንግሥትም መታሰብ ይኖርበታል። “ብቻ ወያኔ ይውደቅልን” ፉከራ፡ ድርጅት ይዞ “ትግሉን ምሩኝ” ባይ ፖለቲከኛ፡ ዒላማና ግቡን ያላገናዘበ ስብስብ፡ መነሻና መድረሻው የተዘበራረቀበት ከመሆን ባሻገር ትግሉ ላይ በረዶ እየነሰነሰ መሆኑን ማጤን ግድ ይላል።

የሀገራችንን የዘመናት ውስብስብ ችግር ለመፍታት ችግሮቹን ጠንቅቆ መረዳትና መደረግ ያለበትን ከተጨባጩ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በመዳሰስ የመፍቻውን ቁልፍ በጋራ ለማዘጋጀት ቅንነትን መላበስ እንደሚገባ ታጋይ ድርጅቶች ሊያጤኑት ግድ ይላል። ለዘመናት ለሰለቸው ጨኸትና ባዶ መፈክር፡ ለአዋጅ ጋጋታ መዘጋጀት ሳይሆን በቅንነት መመካከርን፡ መምከርን ይጠይቃል። ሀገራችን ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ ተገንዝቦ በጋራ ለመምከር ከመጣር ይልቅ ብቻዬን ወይም ከተስማሙኝ ጋር ብቻ እጓዛለሁ ባይነትን የተላበሰ ሌላውንም ገፍቶ እራስን የማግለል ሩጫ የተላበሰ/ሱ ተቃዋሚ ኃይሎች በቀጣይነት ትርምስ ፈጣሪ እንጂ ሀገር መሪ፡ መብት አስከባሪ፡ ለሀገርና ሕዝብ አሳቢ መሆናቸው ያጠራጥራል። ዛሬ ማንንም ሳያገል በአንድ ጠረጴዛ

*ዙሪያ ተቀምጦ ሊመክር ያልቻለ ኃይል ከወያኔ ውድቀት በኋላ እሩጫው "ለዜሮ ፊታውራሪነት" (የጎመጀውን ደረጃ) መሽቀዳደም እንደሚሆን መናገር ትንቢተኝነትን አይጠይቅም። አንዱ "የብሔር/ብሔረሰቦችን መብት ሕዝቡ ይወስን"፡ ሌላው መሳሪያውን ተማምኖ "የምን ውሳኔ ልገንጠል"፡ ሌላው ሌሎች ዘፍነው ያልሆነላቸውን የዱላ አንድነት ሲደግም፡ ከዋናው መግባቢያ አጀንዳና ከትልቁ የሀገራችን ሥዕል ይልቅ በልዩነት ላይ ሲነታረኩ ጀምበር ጠልቃ ሀገር ወደ ጥፋትና መበታተን ጎዳና ልታመራ እንደምትችል ወያኔ ከቀበረው የዘር ፈንጂ ባሻገር እኛም የምናቀጣጥላቸው በርካታ ምልክቶች መኖራቸው አጠያያቂ አይደለም።*

*ሁሉንም ብሔር/ብሔረሰቦች በአንድነት ይዞ ለጋራ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መታገል ሲቻል፡ የግንጠላ ዓላማ የተጠናወታቸውን ብቻ ይዞ "ወደፊት ሕዝብ ይወስናል" ማለት እሳት ላይ ቤንዚን መጨመር ነው። ሊቆጣጠሩት የማይችሉት እሳት በሀገር ላይ ለመለኮስ መንደርደር፡ ማቆሚያው የማይታወቅን የርስ በርስ ግጭት ለመጫር ፍላጎት ላለው ወያኔ መመቻቸት ነውና አጥብቀን ማውገዝ ይጠበቅብናል። ደርግን ለመጣል በሻቢያና በወያኔ የተደረገው የጋራ ትግል ደርግን ጥሎ አላበቃም። "ደርግ ይውደቅልን ብቻ" ያሉትም "ሕዝብ ይወስን" በሚል ፈሊጥ በግርግር "ነፃነት ወይስ ባርነት" ብለው ኤርትራን ከአሰብ ችሮታ ጋር አስወስደዋታል። በዚህ ሀገር የማስገንጠል ጉሮ ወሸባዬ በአሜሪካና እንግሊዝ አቀነባባሪነት የኦነግን አጃቢነት አስታኮ የሎንደኑ ጉባኤ ኤርትራ እንድትገነጠል ሲዶልት ዓላማቸው አድርገው ከተነሱት ወያኔና ሻቢያ ባሻገር ለመጣው ሁሉ መስገድ የማያሳፍራቸው፡ አንዳንድ አድርባይ ምሁራን ታዲያ ዋናው የቲያትሩ ገጸ ባህሪያት ነበሩ። አሁንም የምናየው ይህንኑ ነው።*

*በአሁኑ ጊዜ በተቃዋሚው ጎራ በኩል ያለው ጥያቄ ለምን ግብንቦት 7 ከኦነግና ከኦብነግ ጋር ተነጋገረ አይደለም ጉዳዩ። ኦነግ ቢዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የጋራ ግንባታ እስካመነና በዚህ ጉዳይ ከግንቦት 7 እስከተስማማና መተማመንን ከፈጠረ ከሌሎች የአንድነት ኃይሎች ይህን መተግበር ምን ያቅተዋል? ከአንድነት ኃይሎች ጋር በሚደረግ የጋራ ትግል የኦሮሞም ጥያቄ ይሁን የሁሉም ኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ይፈታል የሚል እምነት ከተላበሰ በአንድነት እምዬ ኢትዮጵያ ብሎ እንደ ኦሮሞ ልጆቹ ለምን አይሰለፍም? ይህ ነው ቁልፍ ጥያቄ። ዛሬ የወያኔ መጨረሻው ነውና ከአመቻችን ጋር ግንባር ፈጥረን ከወያኔ ውድቀት በኋላ "ወደፊት ሕዝብ ይወስናል" እንዳልነው ለኦሮሞ ብሔር "ነፃነት ወይስ ባርነት" የሚለውን ምርጫ ሰጥተን እኛም ተራችንን የለንደኑን ጉባኤ ደግመን ኢትዮጵያን በያቅጣጫው እንበትናለን ጉዞ የህልም ሩጫ እንደሚሆን መጠራጠር አይግባን። ጉዳዩን በሚገባ የተረዱ የአንድነት ኃይሎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላ በየሥፍራው ይህን በሀገርና ሕዝብ ላይ ዳግም ቁማር ለመቆመር የተዘጋጀን የጥፋት ኃይል ማጋለጥና መቃወም ብቻ ሳይሆን ሂደቱን ሊመክቱት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።*

*አግባብ የሌለው ሥራ ሲሰራና ተቀባይነቱ እየሳሳ ሲመጣ እየታየ በአንዳንድ ተማርን ባሉና የፖለቲካ ዝና ፈላጊ ወገኖች ለማደናገሪያ የሚወረወሩ አባባሎችና ጽሁፎች አንደምታው ሌሎችን የመናቅ አዝማሚያ፡ የፖለቲካ ባዶነት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓይኑ ሲመለከት የኖረውን ሐቅ ሸፋፍኖ፡ መገለጽ የሚገባቸውን ኩነቶች በትክክለኛ ገጽታቸው እንደማቅረብ ፈንታ፡ እያድበሰበሱና*

*እየሸፈጡ መናኛና አዘናጊ ዲስኩር አምኖ ይቀበለናል ማለት አደገኛ ሞኝነት ነው። ጊዜን እየጠበቁ ታሪክን በዘፈቀደ መተርጎም፣ ለዛሬው እንቅስቃሴ ይረዳኛልና ትላንት ያልኩትን ትቼ ሌላ ብሆን፣ እያሉ እንደ እስስት የተቀያየረ፣ ዒላማውን የማይመታ ዓላማ ቢስ ሂደት ሊጤን ይገባዋል። ነባራዊውን ሁኔታ በማጭበርበር፣ ሕዝባዊ ቃላቶችን ያለቦታቸው በመሰንቀር፣ ድብቅ ዓላማን ለማስፈጸም በማር የተለወሰ መራርን ማቅረብ ተቃዋሚ ነን ብለው በተነሱ የትግል እንቅፋቶች ሲደገም ማየቱ ከደርግና ወያኔ የተጋባ በሽታ መሆኑን ከተረዳን ሰንብተናል። የአንድነት ኃይሉን ለመከፋፈል ካላቸው ዕኩይ ተግባር አንፃር ቀና ብሎ ያላያቸውን ከኛ ጋር ወስኗል ሲሉ አለማፈራቸው የማንነታቸው መግለጫ ነው። መራራው ትግል ሲሰለቻቸው የሌሎችን መለስተኛ ልዩነቶች ያራግባሉ።*

*መገነጣጠል ዒላማቸው አድርገው ከተነሱ ኃይሎች ጋር የተጀመረው መድረክና ትቅቅፍ አንድነት ኃይሉን ለማግባባትና፣ ለማቀራረብ፣ ለማስተባበር የታቀደ ሳይሆን የአንድን ብሔረሰብ አባላት ከሌላው ለማባላት የታቀደና ኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረ በባዕድ ኃይሎች የሚቀነባበር ዳግማዊ የለንደን ጉባኤ ቅድመ ዝግጅትን በጋራ ልንቃወመው ይገባናል። የጎላ የብሔር ትምክህት የሚያጠቃቸውና ታሪክን በትክክለኛ መልኩ እንዳያዩ አወቅሁ፣ ተማርሁ ባይነት ያደነቆራቸው አንዳንድ “ምሁራን” ኢትዮጵያዊነት ላይ እየዘመቱ ይገኛሉ። ስለ ኢትዮጵያ ከማውራት ይልቅ ወከልኩ ያለውንም ብሔር ድጋፍ የሌለውን “የኦነግ አፈ ጉባኤ”፣ “የኦነግ ገደል ማሚቶዎች” ሆነው ተሚጋች ሲሆኑ ይታያሉ። “የምጣዱ እያለ …” እንዲሉ የኦነግ አመራር አባላት እንኳ ባገኙት መድረክና አጋጣሚ የነኚህን ተገለባባጭ፣ ሙልጭልጭ ምሁራን ያህል ደፍረው አልተናገሩም። “ዓመል ያወጣል ከመሀል” እንዲሉ ዓመላቸው ከትግል ሜዳ የወረወራቸው ለስማቸውና ለተጠናወታቸው ዝና ፍለጋ በግብጽና ቱኒዝያ ሲጎመጁ ይደመጣሉ። አድፍጠው ያደቡና አመቺ አጋጥሚ የመሰላቸውን ሲያገኙ ደግሞ ያለኛ መሪና ተደማጭ አይኑር ይላሉ። ከወያኔ የ5 ዓመት ምርጫ ትርዕይት በኋላ ተደላድለው ይቀመጡና ሌላ ዙር ምርጫ ሊዳረስ ሁለት ዓመት ሲቀረው ብቅ ሲሉ ሌላውም “እንያቸው፣ ተዋቸው” ሲል ተመሳሳይ አዙሪት ውስጥ እየተደጋገመ ሲገባ ያሳዝናል። የወያኔ ምርጫ አጃቢዎችስ ተልዕኳቸው “ትግል በቀጠሮ” መሆኑ ሳያንስ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ሌላው ኃይል ቁጭ ብሎ ሲጠብቃቸው አንዴ ኤኤፍዲ አንዴ ጥምረት እያሉ ስምና ዓርማ እየቀያየሩ ያንኑ ባህሪያቸውን በስሌት ሲመግቡን መጥገባችንን፣ መንገፍገፋችንን በዘራፍና በወሬ ሳይሆን በተግባር ማሳየት ከተሳነን የዚች ሀገር መከራ ማብቂያው ቀላል መሆኑ ያጠራጥራል።*

*አሁን አሁን አንዳንድ ግለሰቦችም ሆኑ በፖለቲካ ድርጅት የታቀፉ ኃይሎች በየጊዜው የሚነሱትን በትግል ስም ደንቃራዎችን “እስቲ እንያቸው” ፈሊጥ እራሱን የቻለ ችግር አለው።* AFD *ተመስርቶ ሲያተራምስ እስቲ እንያቸው ባዮች የማይጠበቁና የማይታሰቡ ግለሰቦች ነበሩ። በምርጫ* 2002 *ተዋናይ የነበሩትን አንጋጠን ስናይ ያለነው ወደ ኋላ መሆኑን እንኳ መገንዘብ አቅቶን ዛሬም ሌላ ትያትር እንድናይ እንገደዳለን። በተቃዋሚ ስም የተነሳን ሁሉ የመንደፍ ፍላጎት ሳይሆን መሠረታዊ የሀገር ህልውና ጉዳይ ሲጣስ ግን ድምጽ ማሰማት፣ ብዕርን ከወረቀት ማገናኘት ግድ ይላልና ነው።*


የሎንደኑ 1983 ዓ.ም. ስምምነት አንድነት ኃይሉን አግልሎ ባይሳካለትም ሌላ መገንጠል ዓላማ ይዞ የሚጓዘውን ኦነግን አሳትፎ በውጭ ኃይሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ተሳትፎ ሕዝብ ሳይመክርበት ኤርትራ በግርግር ከመገንጠሏም አልፋ አግባብነት የሌለው አሰብ ተችሯታል። በተመሳሳይ መልኩ የአንድነት ኃይሉን አግልሎ ኢትዮጵያን ለመበታተን ከሚጥሩት ባዕዳን ኃይሎች ሤራ ሥር ተሰልፎ፡ ወያኔ ተንገዳግዷልና ጊዜው ዛሬ ነው ብለው የህዝብን ስሜትና ብሶት ተጠቅመው ሌላ የግንጠላ ፍላጎታቸውን ሊያረኩ ሲያሴሩ ምነው መተባበር አስፈለገ? የአሰብን ጉዳይ ለመጠየቅ መብት የለኝም ያለው ግንቦት 7 እንገንጠል ከሚሉ ጋር መተባበሩ ከምን የመነጨ ነው?

ከኦነግ ጋር አብሮ መጓዙ አስፈላጊ ነው ከተባለም በዚህ ጉዳይ ምነው በኢትዮጵያ አንድነት ያሉ ታጋይ የፖለቲካ ኃይሎችን በመላ፡ የሀገር ሽማግሌዎችን፡ ታዋቂ ግለሰቦችን፡ ምሁራንን፡ የሲቪክ ማህበራትን፡ ወዘተ. ማካተት አልተፈለገም? ወይስ እነዚህም በስም ብቻ ከሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች ተመድበዋል አለያም ለተያዘው ድብቅ ዕቅድ እንቅፋት ይሆናሉና ነው? ሞኝነት ነው እንጂ በሀገር አንድነት ጉዳይ በአግባቡ ከተሄደ ወከልን ካሉት የኦሮሞ ብሔር እንኳ ድጋፍን አያገኙም። “እየዬ ሲዳላ ነው” እንደተባለው ለቀጣይ መበታተን ቀጣይ ሴራ በሻቢያና በፀረ-አንድነት ኃሎች ሲፈተል ጥጥ ከመደወር ይልቅ የአንድነት ኃይሉ ይሰባሰብ ዘንድ መጣሩ ይመረጣል። ያለንን ዕውቀትና ችሎታ ለሀገርና ህዝብ አንድነት ብንቸረው፡ ብናቃጥለው፡ ብናጠፋው ይመረጣል። በቃ ብለን ለመነሳት መጀመሪያ ማብቃት ያለብን የተጠናወተንን ቅዠት ነው። በቃ ከተባለ መጀመሪያ መብቃት ያለበት የአንድነት ኃይሉ በሆነው ባልሆነው መባላት ነው። መብቃት ያለበት የአንድነት ኃይሉ ጎራ ለይቶ እርስ በርስ የሚያደርገው ሹክቻ ነው። መብቃት ያለበት የአንድነት ኃይሉ መበታተን ነው። መብቃት ያለበት ከሕዝብ በስተጀርባ የሚሸረቡ ተንኮሎች ናቸው። መብቃት ያለበት የኢትዮጵያን አንድነት ከሚፈታተኑ ባዕዳን ኃይሎች ጉያ መወሸቁ ነው። ይህ ሲሆን ሀገርን ለማዳን ዝግጁ ነንና ዳር ቆሞ የሚታዘበንም የኅብረተሰብ ክፍል እሰየው ይላልና፡ ወያኔም ይደነግጣልና ብንጥለውም ቀጣይ ትግሉን ለመምራት ዝግጁ ነንና እሰየው ያሰኛል።

ሀገራችን ባለችበት በዚህ አስጊ ሁኔታ፡ ተቃዋሚው ኃይል በጋራ ተሰባስቦ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግር በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለመፍታት፡ ትምክህተኝነትን ተዋግቶ፡ የብሔር ጥላቻን ተቃውሞ መነሳት ሲገባው፡ አንዳንዱ አልፎ ተርፎ መሐል ገብቶ የዘር ፖለቲካን አራጋቢ መሆኑ በታሪክ የተለመደ ቢሆንም አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑ አልቀረም። ከባዱን ፈተና እንዳይቋቋም እንደ ውርዴ ተደብቆ የሚኖረው አንዳንድ ምሁር ጠባዩ ያገረሸበታል። የላላው የዕውቀቱ ልጓም አልገታው ካለ፡ በሀገሪቱ ላይ የሚጠናከረው የአንድነት ወላፈን እንደሚያነቃው ተስፋ አለን።

መገነጣጠል የሀገር መከፋፈል፡ በኢኮኖሚና በሌሎች መስኮች ያለውን ችግር ስለሚያባብስ ተፈላጊዎቹ ግዴታዎችና፡ መሠረታዊ ጥያቄዎች እስከተሟሉ ድረስ ኢትዮጵያችን የሁሉም ልጆቿ መሆኗ ዘላቂ ጥቅምን ከመስጠቱም ባሻገር ክብርና ኩራታችን ነውና መደገፍ አለበት እንላለን።

**ለመቅደም መንሰፍሰፍ (ዜሮ __ፊት አውራሪ)  ከ ኃይሉ (ገሞራው)**



**ለቁንጮ መንሰፍሰፍ ፡ ለግንባር መንሰፍሰፍ**
**የባሕሪ ሆኖ መሽቀዳደም ለጫፍ**
**በስንቱ ላይ ታይቷል ፡ በታሪክ ምዕራፍ።**

**ከሰው ተለይቼ ፡ ከብሬ ልቀመጥ፡**
**ቀድሜ ልውጣ ሲል ፡ ስንቱ ታይቷል ሲፈርጥ**
**በመጥፎ አወዳደቅ ፡ ወርዶ ሲፈጠፈጥ።**

**ካለፉ ታሪኮች ፡ ቀስሞ ተመክሮ**
**መጠንቀቅ ሲገባው ፡ አውቆና ተምሮ**
**ከፊት ልቅደም ይላል ፡ ስንት ድምባዣም ዜሮ።**

**አግድም ብቻ ሳይሆን ፡ ሽቅብ ልቅደም ይላል**
**ልንከባለል ባዩ ዜሮ አባ ድብልቡል**
**እሱ ምንቸገረው ፡ ተፈጥሮው ባዶ አይደል**
**ክብደት የለሽ ነገር የሚነጥር የሚዘል።**

**ተው ይቅርብህ ሲሉት ፡ የሰው ምክር ካልሰማ**
**ለምን አይከሠከስ ፡ ልውጣ ሲል ከማማ።**

**ኢትዮጵያ ትኑር ለዘላለም** !!!

**አሉላ** (alulla2@yahoo.com)
**ሰኔ** 16 **ቀን** 2003 **ዓ.ም**. (June 23, 2011)